Asylum Support Partnership
help and advice

refugee action | North of England Refugee Service | Refugee Council | scottish refugee council | Welsh Refugee Council Cyngor Ffoaduriaid Cymru

March 2010 Amharic

# የገንዘብ እርዳታ ብቻ ለማግኘት ማመልከት፡ ከቤተሰብ ወይም ጓደኛ ጋር መኖር

በአሁኑ ጊዜ ከ የእንግሊዝ አገር የዶብ ማህበር (UK Border Agency - UKBA) ጽህፈት ቤት የሚሰጡት የመኖርያ ቤትና የገንዘብ እርዳታ እየተቀበሉ ሆነው ከቤተሰብዎ ወይም ጓደኛዎ ጋር መኖር ስለፈለጉ ከተሰጥዎት የመኖርያ ቤት ለመውጣት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ጽህፈት ቤት ከመውጣትዎ በፊት አስቀድመው ለUKBA ማሳወቅ ይገባል። በ UKBA ጽህፈት ቤት የሚሰጡት የጊዝያዊ መኖርያ ቤቶች ላይ እየኖሩ ከሆነ ደግሞ ለመኖርያ ቤቱ አቅራቢው ማሳወቅ ይገብዎታል። ይህ ካላደረጉ UKBA የሚሰጥዎትን የገንዘብ ድጋፍ ሊያቋርጠው ይችላል።

ይህ በራሪ ጽሁፍ ቀጥሎ ስላሉት ነገሮች ማብራርያ ያቀርባል፡

- ከሚኖሩበት ቤት መቀየር እንዴት ከ UKBA ጽህፈት ቤት የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፍ ሊነካው እንደሚችል
- ቤት ከመቀየርዎ በፊት ምን ማድረግ እንዳለብዎት
- ከቤተሰብ ኣባልዎ ወይም ጓደኛዎ ጋር ለመኖር እንዴት ከ UKBA ጽህፈት ቤት ፍቃድ ለመጠየቅ እንደሚችሉ
- የሚጠይቁትን ጥያቄዎች ለማቅረብ ምን አይነት ሰነዶች እንደሚያስፈግዎት እና
- እንዴት ልንረዳዎት እንደምንችል

## ከቤተሰብ ወይም ከጓደኛየ ጋር መኖር ከፈለግኩ ከ UKBA ጽህፈት ቤት የማገኘውን የገንዘብ ድጋፍ ሊነካው ይችላልን?

የ UKBA ጽህፈት ቤት የቤተሰብዎ ወይም ጓደኛዎ የኪራይ ወይም ሌሎች ሂሳቦች በተመለከተ ምንም አይነት ክፍያ እንደማያደርግ እባክዎን ያስተውሉ። ስለሆነም ቤተሰብዎ አባል ወይም ጓደኛዎ የኪራይ ወይም ሌሎች የቤቱ ወጪዎችን ክፍያ እንዲከፍሉለት መጠበቅ የለበትም።

## ቤተሰቦቼ ወይም ጓደኞቼ በሌላ የእንግሊዝ አገር ክፍል የሚኖሩ ከሆነ ወደዛ በመሄድ ከነሱ ጋር መኖር እችላለሁኝ?

አዎ፣ ሌላ አከባቢ ወደሚኖሩት ቤተሰቦችዎ ወይም ጓደኞችዎ በመሄድ ከነሱ ጋር እንዲኖሩ ፍቃድ ሊጠይቁ ይችላሉ። ነገርግን ወደ ሌላ የእግሊዝ አገር ከተማ ወይም ክፍል በመሄድ ከሌላ ሰው ጋር መኖር የሚፈልጉ ከሆነ፣ ያቀረቡት የኢምግሬሽን ጥያቄዎ ወደ ሚሄዱት ከተማ መሽጋገርና ወደ ሌላ ክፍለ ሃገር ሪፖርት የሚያደርጉ መሆንዎን ማወቅ ይገባል።

**ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ ከUKBA ጽህፈት ቤት ፍቃድ የሚያስፈልግበት የእንግሊዝ አገር ክፍል ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ ጽህፈት ቤቱ በጽሁፍ የሚሰጥዎት ፍቃድ ሳያገኙ መንቀሳቀስ የለብዎትም። ይህ ፍቃድ ሳያገኙ ከተንቀሳቀሱ ባቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ላይ ችግር ሊያመጣቦት ይችላል።**

**መኖርያ ቤት ከመቀየርዎ በፊት ከ UKBA ጽህፈት ቤት በጽሁፍ የሚሰጥ ፍቃድ የሚያስፈልግዎት ወይም የማያስፈልግዎት መሆኑን እርግጠኛ ካልሆኑ፣ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የስደተኞች ማህበር በመሄድ ምክር ማግኘት ይችላሉ።**


British Refugee Council, (commonly called the Refugee Council) is a company limited by guarantee registered in England and Wales, [No 2727514] and a registered charity, [No 1014576].
Registered office: 240-250 Ferndale Road, London SW9 8BB, United Kingdom, VAT no: 936 519 988

OISC No: N200100132 | Community Legal Service

## መኖርያ ቤት ከመቀየረ በፊት ሌላ ላደርገው የሚገባኝ ነገር አለን?

- **ክፍል 55 (Section 55) (ይህ ህግ የ UKBA ጽህፈት ቤት የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ የማቋረጥ መብት የሚሰጥ ህግ ነው)**

ወደ እንግሊዝ አገር ከገቡ ወዲህ ከሰዎስት ቀናት (72 ሰአቶች) በኋላ የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገቡና እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ብቻ እንዲሰጥዎት የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ይህ ከ UKBA ጋር በሚደረገው የክፍል 55 (Section 55) ቃለ መጠይቅ እንዲሳተፉ ሊደረግ ይችላል።

በዚህ ቃለ መጠይቅ ጊዜ ላይ UKBA ቀጥሎ ያሉትን ነገሮችን ይመለከታል፤

- የጥገኝነት ማመልከቻዎ በተቻለ መጠን በጊዝየው እንዳመለከቱ
- አመጣጥዎን በተመለከተ የሰጡትን መረጃ የሚታመን ሆኖ ካገኙት
- የ UKBA ጽህፈት ቤት እርስዎን ድጋፍ መስጠት ከከለከልዎት በእርስዎ ላይ ኢሰብኣዊና አዋራጅ የሆኑ ሁኔታዎች ይወርድቦታል ወይ የመሳሰሉትን ይመለከታሉ።

የ UKBA ጽህፈት ቤት እርስዎ በጊዝየው ('በተቻለ መጠን በመፍጠን') የጥገኝነት ማመልከቻዎ ኣላስገቡም ብሎ ከወሰነ፣ የሚሰጡትን የገንዘብ ድጋፍ ከማግኘት ሊከለክልዎት ይችላሉ። ይህንን ውሳኔ በተመለከተ ይግባኝ ለማለት ኣይችሉም፣ ሆኖምግን እንደገና ውሳኔው እንዲታይሎት ሊጠይቁ ይችላሉ።

- **የህግ ምክር ማግኘት**

ወደ ሌላ የእንግሊዝ አገር ክፍል ከተንቀሳቀሱ፣ በዚህ ጊዜ ያለውን የሕግ አማካሪዎ እርስዎን መወከል እንደማይቀጥሉ ሊነግርዎት ይችላሉ።

ስኮትላንድ ከሌሎች የእንግሊዝ አገር ክፍሎች የተለየ የህግ አሰራር አላት። ጉዳይዎ በህጋዊ ግምገማ (Judicial Review) ላይ ከሆነ ወይም በስኮትላን ፍርድ ቤት ክፍል (Court of Session in Scotland) ስር ከሆነ፣ ወደ ሌላ የእንግሊዝ አገር ክፍል ለመንቀሳቀስ ፍቃድ እንዲሰጥዎት ከመጠየቅዎ በፊት ከህግ አማካሪዎ ጋር እንዲመካከሩ በጥብቅ እንመክሮታለን።

- **የጉዞ ወጪዎች**

ለመንቀሳቀስ ከወሰኑ፣ የጉዞው ወጪዎችን በተመለከተ የ UKBA ጽህፈት ቤት ምንም አይነት እርዳታ አይሰጥዎትም ሁሉም ወጪዎች ራስዎ የሚሸፍኑት መሆንዎን ማወቅ ይገባል።

## ከምንቀሳቀሴ በፊት ከ UKBA ጽህፈት ቤት ፍቃድ የሚያስፈልገኝ ከሆነ አስቀድሜ ምን ማድረግ ይገባኛል?

ወደ የUKBA ጽህፈት ቤት የራስዎ ፊርማ ያለበት ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ ይገባል። በተጨማሪም ከቤተሰብዎ ወይም ከጓደኛዎ እርስዎ ከነሱ ጋር ለመኖር ፍቃደኛ መሆናቸውን የሚገልጽ በጽሁፍ የተሰጠ ማረጋገጫ ማቅረብ ይገባል።

መኖርያ የሚሰጥዎት የቤተሰብዎ አባል ወይም ጓደኛዎ የራሱ የሆነ የመኖርያ ቤት ካለው ቀጥሎ ያሉትን መረጃዎች የያዘ ደብዳቤ ማቅረብ ይገባል፡

- የባለቤትነት ማረጋገጫና እርስዎ ከእነርሱ ጋር እንዲኖሩ የሚፈቅዱ መሆናቸውን
- ለቤት ኪራይ ወይም የጋዝ፣ ኤሌክትሪሲቲና ውኅ (ሂሳቦች ተብለው የሚጠሩ) ለመሳሰሉት ወጪዎች እርስዎ ምንም እንደማይከፍሉ እና
- የመኖርያ ቤት ብቻ እንጂ ሌላ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ እንደማይሰጥዎት መግለጽ ይገባቸዋል።

በተጨማሪም ቀጥሎ ያሉትን ማቅረብ ይገባቸዋል፥

- ትክክለኛ ሥምና ኣድራሻ የሚገልጽ የሂሳብ (ጋዝ፣ ኤሌክትሪሲቲ፣ ውኅ) ወቅታዊ ደረሰኝ፣ እና
- የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ፣ ለምሳሌ የሞርጌጅ ክፍያዎች።

የቤተሰብዎ አባል ወይም ጓደኛዎ መኖርያ ቤቱን ተከራይተውት ከሆኑ፣ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች ማቅረብ ይገባቸዋል፥

- በተገለጸው ቤት እርስዎ ከጓደኛዎ ጋር እንዲኖሩ የሚፈቅድ መሆኑን የሚያሳይ ከቤቱ ባለቤት የተፈረመ ደብዳቤ
- መኖርያ የሚሰጥዎትን ጓደኛዎ እርስዎ የቤት ኪራይ ወይም ሂሳቦች (የጋዝ፣ ኤሌክትሪሲቲና ውኅ) ለመሳሰሉት ወጪዎች እርስዎ ምንም እንደማይከፍሉ የሚያረጋግጥ የተፈረመ ደብዳቤ እና
- ሥምና አድራሻን የሚያረጋጥ በቅርቡ የተከፍለ ደረሰኝ።

**እንዴት ልንረዳዎት እንችላለን?**

የስደተኛ ኤጀንሲዎች እርስዎ ከቤተሰብዎ ወይም ጓደኛዎ ጋር እንዲኖሩ ወደ የ UKBA ጽህፈት ቤት የሚያደርጉት የጽሁፍ ማመልከቻ እንዲጽፉ ሊረዳዎት ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የUKBA መኖርያ ቤት የሚያቀርብሎት ክፍል፡ አከባቢው የሚገኙት የስደተኛ ኤጀንሲዎች እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉ ሊነግርዎት ይችላል ወይም ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ ያለውን ድህረገጽ በመጠቀም ኣድራሻዎቹን ለማግኘት ይችላሉ።

ለ UKBA ጽህፈት ቤት ስለ አዲሱ አድራሻዎ ወይም የሚከሰቱት የሁኔታዎች ለውጦችን ለማሳወቅ ከፈለጉ፣ አቅራብያዎ የሚገኝ የስድተኞች ኤጀንሲ ለማነጋገር ይችላሉ።

**ቀጥሎ ምን ይሆናል?**

ከቤተሰብዎ ወይም ጓደኛዎ ጋር ለመኖር ፍቃድ እንዲሰጥዎት በሚያመለክቱበት ጊዜ የ UKBA ጽህፈት ቤት ፍቃዱ ለማጠናቀቅ ሳምንቶች ሊወስድ ይችላል። የ UKBA ጽህፈት ቤት የወሰዱት ውሳኔ ምን እንደሆነ ለማሳወቅ ደብዳቤ በቀጥታ ወደ እርስዎ ይልክልዎታል።

በአራት ሳምንት ውስጥ ከ UKBA ጽህፈት ቤት ምንም ደብዳቤ ካልተቀበሉ፣ እባክዎን ከስደተኛ ኤጀንሲው አንዱን ያነጋግሩ።

ያቀረቡት የመንቀሳቀስ ጥያቄ ከተፈቀደ፣ የ UKBA ጽህፈት ቤት በቀጥታ ደብዳቤ በመላክ መቀየር የሚፈልጉት መቼ እንደሆነ ቀኑን ለይተው ጽህፈት ቤቱን እንዲያሳውቁ ይጠይቅዎታል። ከዛ በኃላ የሚላኩት ደብዳቤዎች ወደ አዲስ አድራሻዎ ይላካሉ።

ከቀየሩ በኃላ ድጋፍዎን በተመለከተ የሆነ አይነት ችግር ካጋጠምዎት፣ የድሮ የስደተኛ ኤጀንሲ ሳይሆን አዲሱ መኖርያ ቤትዎ አቅራብያ የሚገኝ የስደተኛ ኤጀንሲውን ማነጋገር ይገባል።